የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፹፪
አዲስ አበባ ሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 82
ADDIS ABABA 8th July 2011

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፵፰/፪ሺ፫

የኢትዮጵያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........................ ገፅ ፮ሺ፫

## CONTENTS

Regulation No. 248/2011

Ethiopian Road Construction Corporation Establishment Council of Ministers Regulation ..................... Page 6003

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵፰/፪ሺ፫

### የኢትዮጵያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵፰/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. መቋቋም**

፩/ የኢትዮጵያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ) የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

**፫. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

የትራንስፖርት ሚኒስቴር የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

**፬. ዋና መስሪያ ቤት**

የኮርፖሬሽኑ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 248/2011

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN ROAD CONSTRUCTION CORPORATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 47(1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. ***Short Title***

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Road Construction Corporation Establishment Council of Ministers Regulation No. 248/2011".

2. ***Establishment***

1/ The Ethiopian Road Construction Corporation (hereinafter the "Corporation") is hereby established as a public enterprise.

2/ The Corporation shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

3. ***Supervising Authority***

The Ministry of Transport shall be the supervising authority of the Corporation.

4. **Head Office**

The Corporation shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as necessary.

**፭. ዓላማ**

ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ የሥራ ተቋራጭ ሆኖ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር መንገዶችን፣ ድልድዮችንና ሌሎች የሲቪል ግንባታ ሥራዎችን በመስራት፣ በማሻሻልና በመጠገን ሥራዎች ላይ መሠማራት፤

፪/ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችና ማሽነሪዎች የጥገና አገልግሎት መስጠት፤

፫/ የግንባታ ዕቃዎችንና ማሽነሪዎችን ማከራየት፤

፬/ የኮንስትራክሽን ማቴሪያሎችን ማምረትና መሸጥ፤

፭/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎች ማካሄድ፡፡

**፮. ካፒታል**

የኮርፖሬሽኑ የተፈቀደ ካፒታል ብር ፪ቢሊዮን ፭፻፶ ሚሊዮን (ሁለት ቢሊዮን አምስት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፩ቢሊዮን ፰፻፮ ሚሊዮን ፰፻፫ሺ፯፻፷፰ (አንድ ቢሊዮን ስምንት መቶ ስድስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሦስት ሺ ሰባት መቶ ስልሳ ስምንት ብር) በጥሬ ገንዘብና በአይነት ተከፍሏል፡፡

**፯. ኃላፊነት**

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በእዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

**፰. ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ**

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

**፱. የመብትና ግዴታ መተላለፍ**

ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የኦፕሬሽን ዘርፍ ጋር የተያያዙ የባለሥልጣኑ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል፡፡

**፲. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

**መለስ ዜናዊ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ጠቅላይ ሚኒስትር**

**5. *Purposes***

The purposes for which the Corporation is established are:

1/ to engage in domestic and overseas construction works as a contractor in constructing, upgrading and maintaining roads, bridges and other civil works;

2/ to engage in the business of maintaining construction equipment and machinery;

3/ to engage in the rental business of construction equipment and machinery;

4/ to produce and sell construction materials;

5/ to undertake in any other related activities necessary for the attainment of its purposes.

**6. *Capital***

The authorized capital of the Corporation is Birr 2,550,000,000 (Two Billion Five Hundred Fifty Million Birr) of which Birr 1,806,803,768 (One Billion Eight Hundred Six Million Eight Hundred Three Thousand Seven Hundred Sixty Eight Birr) is paid up in cash and in kind.

**7. *Liability***

The Corporation shall not be liable beyond its total assets.

**8. *Duration of the Corporation***

The Corporation is established for indefinite duration.

**9. *Transfer of Rights and Obligations***

The rights and obligations of the Ethiopian Road Authority relating to its operation department are hereby transferred to the Corporation.

**10. *Effective Date***

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 8th day of July, 2011.

**MELES ZENAWI**
**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**